ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የቃላት አገባብ ስርዓትን ተከትለው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- ለውስብስብ ቃላት ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ ያሉትን ስርዓተ ነጥቦች በተገቢው መንገድ ይጠቀማሉ፡፡
- ቃላትን እየነጣጠሉ ያነባሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡- ➢ አዳምጠውየምንባቡን መልዕክት ይገልጻሉ፡፡ ➢ በትክክል ያነባሉ፡፡ ➢ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡የተሰጣቸውን አረፍተ ነገርተጠቅመው አንቀጽ ይመሰርታሉ፡፡ ➢ የወልና የተጸውኦ ስሞችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡	➢ ማዳመጥ እና መናገር ➢ ማንበብ ➢ ቃላት ➢ መጻፍ ➢ ሰዋሰው	ተማሪዎች የቃል ቅርጽንና የፊደል አሰዳደርን እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡ ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላትን እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡ ቃላትን ቅርጻቸውን መሰረት በማድረግ እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡ ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸውን የቃላት ቅርጾች አንድ ላይ እንዲመድቡ ማድረግ ግልጽ መመሪያ በመስጠትና ምእላዶችን በማብራራት መልመጃ ሰጥቶ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡	➢ ከተማሪዎች መልስና ሀሳብ በመነሳት መምህሩ የትኛው ይዘት ላይ ማተኮር እንዳለበትና እንደሌለበት ይወስናል፡፡ ➢ ከተማሪዎች አቀራረብ በመነሳት የሚያሳዩትን መሻሻልመገምገም ➢ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠታቸውን በመከታተል የቃላት እውቀታቸውን መመዘን፡፡

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ ሁለት፡-ታዋቂ አትሌቶች (18 ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ከቅጥያዎች ውስጥ ዋና ቃል ይለያሉ፡፡
- ቅጥዎችን በማጣመር ቃላት ይመሰርታሉ፡፡
- የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሃሳብ ይገልጻሉ፡፡
- የስርአተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድተው የሚነሱና የሚወድቁ ድምጾችን ይለያሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ ታሪኩን አዳምጠው ድጋሚ ይገልጻሉ፡፡ ➢ ውስብስብቃላትንበማጣመርና በመነጠል ያነባሉ፡፡ ➢ አንቀጽ ይመሰርታሉ ➢ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ ተመሳሳይ ቃላትን ይለያሉ፡፡ ➢ የጥቅል ስሞችን ይለያሉ፡፤	➢ ማዳመጥ እና መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	ያዳመጡትን ምንባብ ደጋግመው በቃል እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ በቃል ያቀረቡትን ንባብ በተመለከተ ግብረ መልስ ከመምህሩ ከተማሪና ከቤተሰብ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡ ያልተለመዱ ቃላትን ማንበብ እንዲችሉ የምእላድ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡ መምህሩ ምልክቶችን በማየት የስርዓተ ነጥቦችን ጥቅም አንዲረዱ ማድረግና ስርዓተ ነጥቦች በአገላለጽ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ አንዲረዱ ማድረግ፡፡	➢ ተማሪዎች የተጠየቁትን ጥያቄ በምልክት ይመልሳሉ፡፡ ➢ **ኢርቱ ክትትል፡-** በዚህ ወቅት መምህሩ ስራ ለተማሪዎች በመስጠት በክፍል ውሰጥ በመዘዋወር ያለውን መሻሻል ይከታተላል፡፡

ምዕራፍ ሶስት፡-ቃላዊ ግጥም (18 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ያወቁትን አዳዲስ ቃላት ይጠቀማሉ፡፡
- ግጥም ጽፈውያነባሉ፡፡
- ቅንፍን በአረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- ገላጭ ጽሁፎችን ተራኪ ጽሁፎችንና የቃል ግጥሞችን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያነባሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው ተመሳሳይ የቃል ግጥም ያቀርባሉ፡፡ ➢ ግጥምን በትክክል ያነባሉ፡፡ ➢ በአረፍተ ነገር ውስጥ ቅንፍና አዝባርን ይጠቀማሉ፡፡ ➢ ለተዘረዘሩ ቃላት ተቃራኒ ይሰጣሉ፡፡ ➢ በአረፍተ ነገር ውስጥ የጊዜ ተውሳክ ግስን ይለያሉ፡፡	➢ ማዳመጥ እና መናገር ➢ ማንብብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	መምህሩ ለተማሪዎች **ምር ጽሁፍ** ለተማሪዎች ምሳሌ የሚሆኑ የደብዳቤ ጽሁፎችንና የተለያዩ የጽሁፍ ቅረጾችን በማምጣት እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ ምሳሌ አድርገው የሚጽፏቸው ጽሁፎችን በመስጠትያንን ተከትለው እንዲጽፉ ማበረታታት ለምሳሌ የአረፍተ ነገር መጀመሪያ ቃላት የቃላት ቅርጽ፡፡ ተማሪዎች እንደ ምርጫቸው እነዲጽፉ እድል መስጠት፡፡ ➢ ተማሪዎች እንደ ጸሃፊ እንዲሳትፉ ማድረግ ➢ ተማሪዎች እርስበርሳቸው ግብረ መልስ እንዲሰጡና እንዲቀበሉ ማበረታታት	➢ አንዱ ተማሪ ለሌላኛው እንዲያነብ በማድረግ ፍጥነታቸውንና የአነባበብ ትክክለኛነታቸውን እንዲተራረሙ በማድረግ ለጽሀፈት እንዲዘጋጁ ማድረግ፡፡ ➢ ለተማሪዎች የመጻፊያ መስፈርት በማውጣት እንዲጽፉ ማድረግ፡፡

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ አራት፡-ዘመናዊ እርሻ (18ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- **አዳምጠው በቃል ይመልሳሉ፡፡**
- **አከራካሪ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡**
- **ቃላትን በመገጣጠም ትርጉምይሰጣሉ፡፡**
- **የጊዜ ግስን ተጠቅመው ዓ.ነገር ይመሰርታሉ፡፡**

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልትና መርጃ መሳሪያ	ምዘና
ከዘህ ትምህረት በኋላተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው መልክቱን በቃል ይገልጻሉ፡፡ ➢ አዳዲስ ቃላትንያፈልቃሉ፡፡ ➢ ለቃላት ፍቺ ለመስጠት ተቀራራቢነት ያላቸውን ቃላት ይጠቀማሉ፡፡ ➢ አከራካሪ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡ ➢ የጊዜ ተውሳከ ግስን ተጠቅመው አረፍተነገርይመሰርታሉ፡፡	➢ ማዳመጥ ና መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	በንባብ ጊዜ እንግዳ የሆኑባቸውን ቃላት ማስታወሻ በመያዝ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ ለተማሪዎችየተለያዩ ስነጽሁፋዊ ዘውጎችን በማቅረብ የኋላ እውቀታቸውን አየተጠቀሙ የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ፡፡ የቅድመ ንባብ ጥያቄ በመስጠት በጥንድና በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ ምንባቡን በዝምታ ንባብ አንብበው ጥያቄዎችን እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡ ምንባቡንበለሆሳስ ንባብ አንብበው ጥያቄዎችን እራሳቸውን ችለው በመመለስ መልሶቻቸውን በራሳቸው እንዲያርሙ ማድረግ፡፡	➢ የተጠየቁትን ጥያቄ መመለሳቸውን ማረጋገጥ፡፡ ➢ ከተማሪዎቹ መለስ በመነሳት የትኛው ይዘት ላይ መተኮር አንዳለበት መምህሩ ይወስናል፡፡ ➢ ባለቀለም ካርድ በመጠቀም መልስ መሰጠታቸውን መከታተል፡፡ ➢ ዓረፍተ ነገሮችን በትክክል መጻፋቸውን ማረጋገጥ፡፡ ➢ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጭብጡን አንዲገምቱ ማድረግ፡፡

ምዕራፍ አምስት፡-ቱሪዝም (18 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ቃላትን በምእላድ ይከፋፍላሉ፡፡
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- በሀላፊጊዜ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ቅድመ ግንድ ቀጥያዎችን ይጠቀማሉ፡፡
- ራስን የመገምገሚያ ስልቶችን ተጠቅመው ራሳቸውን ይገመግማሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልትና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው ቃላትን ወደ ምእላድይከፋፍላሉ፡፡ ➢ አንብበው መልክቱን ይገልጻሉ፡፡ ➢ ለቃላት አመሬያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ ➢ ሃላፊ ጊዜን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡ ➢ ድህረግንድ ቅጥያዎችን ያጣምራሉ፡፡	➢ ማዳመጥና መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰወሰው	መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጽሁፍ መሰረት በማድግ በጋራ አንዲጽፉ ማድረግ፡፡ ድምጽን ከፍ አድርገው የሚያነቡትን ከጽሁፉ ጋር እንዲያያይዙ ማድረግ፡፡ድምጽን ከፍ አድርገው ካነበቡት ውስጥ የራሳቸውን ሃሳብ በማፍለቅ ሪፖረት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ በጽሁፍ ስራ ውስጥ በመሳተፍ እርስበእርስ ግብረመልስ እነዲሰጡና እንዲቀበሉ ማድረግ፡፡ ሲያነቡ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ነገር ካጋጠማቸው እንዲጠይቁ ማበርታታት፡፡ በጽሁፍ ስራ ላይ የሚሳተፍ ማህበረሰብ መፍጠር	➢ አጫጭር ማስታወሻዎችን እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ ➢ በከፊል የተማሩትን ተረድተው ማቅረባቸውን መከታተል፡፡ ➢ የተማሩትንና የተረዱትን መሰረት አድርገው ማጠቃያ አንዲሰጡ ማድረግ፡፡

አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ስድስተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

ምዕራፍ ስድስት፡-ጸረ-አደንዛዥ እጽና ቁሳቁሶች (18 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተከትለው ያነባሉ፡፡
- መረጃ ሰጪ ጽሁፎችን ይለያሉ፡፡
- አዳዲስ ቃላትን ከአገባቡ በመነሳትይገምታሉ፡፡
- አንድን ሀሳብ ለመግለጽ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ ጽሁፉን አዳምጠው ስለጭብጡ ይወያያሉ፡፡ ➢ ጽሁፉን አዳመጠው መልከቱን ከግል ህይወታቸው ጋር አያዘመዱ ይመልሳሉ፡፡ ➢ ለቃላት አማራያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ ➢ ጅምር አንቀጾችን ይጨርሳሉ፡፡ ➢ ተውላጠ ስሞችን ተጠቀመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡	➢ ማዳመጥና መናገር ➢ ማንበብ ➢ ቃላት ➢ መጻፍ ➢ ሰዋሰው	**ግልጽ ማድረግ** ግለጽ ያልሆነላቸውን አንዲጠይቁ ማበረታታት፡፡ **ጥያቄና መልስ** የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ፡፡ **ማሰስ** ጥያቄዎችን ከጸሁፉ እያሰሱ እንዲመልሱ ማድረግ፡፡	➢ **ምልከታ፡-** የተሰጣቸውን ማስታወሻ በትክክል መጻፋቸውን ማረጋገጥ፡፡ ➢ **አቅርቦት፡-** ስራቸውን አንዲያቀረቡ በማድረግ ምን ያህል አንደተረዱ መከታተል፡፡ ➢ **ማጠቃለል** ያዳመጡትን ያነበቡትንና የሰሙትን በማጠቃለያ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ➢ ስለሌላ ሰው ያዳመጡትን አንዲገልጹ ማድረግ፡፡

ምዕራፍ ሰባት የጥላቻ ንግግር(18ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፡-

- መስማማትንና አለመስማማትን የሚገለጹ ሀሳቦችን ያቀርባሉ፡፡
- ምንባቡን በማንበብ የጥላቻ ንግግር አንዴት አንደሚወገድ ይገልጻሉ፡፡
- ቅጽሎችን በመለየት ይጠቀማሉ፡፡
- የጥላቻ ንግግርን አንዴት መከላከል አንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡
- ‹እና›ንና ‹ነገረግን›ን ተጠቅመው ድብልቅ አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው ይመልሳሉ፡፡ ➢ አንብበው ተመሳሳይ ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡ ➢ ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ ➢ ቅጽሎችን ለይተው ይጠቀማሉ፡፡	➢ ማዳመጥ እና መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	በቅድመንባብ ጊዜ በንባብና በድህረ ንባብ ወቅት ቻርቶችን እነዲጠቀሙ ማድረግ፡፡ መረጃዎችን አቀናበርው ማቅረብ የሚያስችሉ የተለያዩ ትልሞችን ማቅረብ፡፡ ኢ-ልቦለዶችንና ሌሎች ታሪኮችን አንዲያነቡ በማድረግ ስለገጸባህሪዎቹ የተረዱትን አንዲገልጹ ማድረግ፡፡ ዋናዋና ዲርጊቶችን የሚገልጽ ቻርት አንዲያዘጋጁ ማድረግ፡፡ ሁነቶችን መረዳት ይችሉ ዘንድ ማን ፤ምን፤መቼ፤የት፤ለምን፤የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችሉ ዋናዋና ዲርጊቶችን የሚገልጽ ቻርት እንዲያዘጋጁ ማድረግ፡፡	➢ መልሳቸውን አጠገባቸው ካሉት ጋር እንዲናበቡ በማድረግ አንዲተራረሙ አድል መስጠት ፡፡ ➢ ቃላትንና ምስልን ተጠቅመው የተረዱትን ማቅረባቸውን መከታተል፡፡

:-

ምእራፍ ስምንት፡- ኤች/አይቪ ኤድስ በኢትዮጵያ(18 ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

የዚህ ምእራፍ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፡-

- በሂደት ባለብዙ ቀጥያ ምእላዶችን ያነባሉ፡፡
- የራሳቸውን አመለካከት ይጽፋሉ፡፡
- የጽሁፍ አላባውያንን ይገልጻሉ፡፡
- ለምእላዶች ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህረት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ የጽሁፉን ዋና መልዕክት ተረድተው ይከራከራሉ፡፡ ➢ የራሳቸውን አመለካከት ይጽፋሉ፡፡ ➢ የጽሁፍ አላባውያንን ይገልጻሉ፡፡ ➢ ለቃላት ተቃራኒ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡ ➢ በተሸጋሪና የመይሻገሩ ግሶች አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡	➢ ማዳመጥ እና መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**መለየት**(ማወዳደር) ተማሪዎች የተሰጣቸውን የሆሂያት መዋቅር መሰረት በማድረግ እንዲያወዳድሩ ማድረግ ይህንንም በሚከተለው መንገድ ማከናወን የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላትን የተሰጣቸውን የቃላት ቅረጽ መሰረት በማድረግ አንድ ላይ በመመደብ ሌሎች ቃላትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡ በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት የቅጥያ ቅርጾችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡	➢ **ክለሳ**፡- ባለፈው የተማሩትን ለክፍሉ አንዲያከፍሉ ማድረግ ፡፡ ➢ **አቅርቦት**፡- ያወቁትንና የተረዱትን አንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ➢ የብጤ እርማት፡-የሰሩትን ወረቀት በመለዋወጥ አርስ በርስ አንዲተራረሙ ማድረግ፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ :-ባህላዊ ልማዶች (18 ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የተስማሙበትን ሃሰብ ያቀርባሉ፡፡
- አጭር ምንባብ አንብበው ወደ ሰንጠረዥ ይቀይራሉ፡፡
- በቃል የሚነበብላቸውን አስተካክለው ይጽፋሉ፡፡
- ከርዕሱ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ስረዓተ ነጥቦችን ጠብቀው ያነባሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ	ምዘና
• ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው ጽሁፉን ይገመግማሉ፡፡ ➢ የጽሁፉን ሃሳብ በቃል ይገልጻሉ፡፡ ➢ ማመልከቻ ይጽፋሉ፡፡ ➢ የሃላፊ ጊዜን ተጠቅመው አረፍተነገር ይመሰርታሉ፡፡	➢ ማዳመጥ እና መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**የቃል ጽህፈት፡-** ተማሪዎች ቃል እያዳመጡ (ታላሚውን የቋንቋ መዋቅር መሰረት ያደረጉ) ቃላትን በመጥራት በቃል እንዲጽፉ ማለማመድ፡፡ **ዓረፍተ ነገር፡-**መምህሩ አረፍተ ነገር በመናገር እንዲጽፉ ማድረግ ፡፡ ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል ፡-አዳዲስ ቃላት የያዙ አረፍተ ነገሮች ቀደም ሲል የተማሩዋቸው ቃላት ተማሪዎች በዚህ ሰአት ተዘውታሪ ቃላት ላይ እያሰመሩ ይሄዳሉ፡፡ **አብነት፡-** የተሻለ የማንበብ ችሎታ ያለውንተማሪ በማቅረብ በምሳሌው መሰረት እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ የተደጋገመ የቃል ንበት ደጋግመው በቃል እንዲያነቡ በማድረግ እርስበርስ የሚተራረሙበትን አድል መፍጠር፡፡	➢ **አካለዊ ምላሽ ዘዴ፡-** የተጠየቁትን በምልክት አንዲመልሱማድረግ፡፡ ➢ **ኢ-ርቱ ክትትል** ፡-አንድ ግጥም ሰጥቶ አንዲያነቡ በማድረግ አነባበባቸውን እየተዘዋወሩ መከታተል፡፡

ምዕራፍአስር፡-ሴቶችን ማብቃት (18 ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የተሰማቸውን ምክኒያታዊ ሆነው ይገልጻሉ፡፡
- አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- የሰው ህይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡
- ስርአተ ነጥቦች ያላቸውን አገልግሎት ተረድተው ያነባሉ፡፡
- ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ዓረፍተ ነገሮችን ይጠቀማሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ ንግግር አዳምጠው ያንጸባርቃሉ፡፡ ➢ የሰው ህይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡ ➢ ቃላትን በምአላድ ይከፋፍላሉ፡፡ ➢ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ አገላለጾችን በአረፍተ ነገር ምሰረታ ወቀት ይጠቀማሉ፡፡	➢ ማዳመጥ እና መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	➢ በቡድን ወይም በተናጠል እየሆኑ ጸሁፉን ተለማምደው ክፍል ውሰጥ እንዲያቀርቡ ማደረግ ይህም ተማሪዎችን ጥሩ ተናገሪና አንባቢ እንደሚያድረጋቸው መገንዘብ፡፡ ➢ ደቂቃ እየያዙ አጫጭር ታሪኮችን በተደጋጋሚ እንዲያነቡ ማድረግ መሻሻሎችን መመዝገቢያ ቻርት ማዘጋጀት ይህንንም በግራፍ ማስደገፍ፡፡ ➢ ቅድመ ጽህፈት ተግባራትን ማለማመድ ይህ ጽህፈት ከመጀመራቸው በፊት የሚከናወን ተግባር ነው በዚህ ስር የታሪክ መዋቅር የቃላት ድር ወዘተ መጠቀም ፡፡	➢ **አቅርቦት፡-** ተግባራቸውን ክፍል ውሰጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ መከታተል፡፡ ➢ **የብጤእርማት**፡-ስራቸውን አየተለዋወጡእንዲተራረሙ ከተደረገ በኋላ ሰበስቦ አርማት መስጠት፡፡ ➢ የቡድን ስራ፡-የቡድን ስራ በመስጠት ሁሉም መሳተፋቸውን መከታተል፡፡

አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ሰባተኛ ክፍል አንደኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

ምዕራፍ አንድ፡ተፈጥሮን ማድነቅ (18) ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ የትምህርት ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የሌሎችን ሀሳብ ያዳምጣሉ፡፡
- ስለተፈጥሮ ምንነት ይወያያሉ፡፡
- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ጽሀፍ ያነባሉ፡፡
- የተፈጥሮን የተለያየ ገጽታ ያደንቃሉ፡፡
- አንቀጽ ይመሰርታሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃመሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ የሌሎችን ሃሳብ በአትኩሮት ያዳምጣሉ፡፡ ➢ የቋንቋውን አውድ ጠብቀው በቋንቋው ይጠቀማሉ፡ ➢ ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መጽሃፍ በትክክል ያነባሉ፡፡ ➢ ተለምዶአዊ ሃሳቦችን ተጠቅመው አንቀጽ	• ማዳመጥ • መናገር • ማንበብ • መጻፍ • ቃላት • ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-ተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ጥያቄ በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ **ለምሳሌ፡- ስለወንዝ አጠቃቀም ምን ታውቃለችሁ፡፡** **የማዳመጥ ጊዜ፡-**መምህሩየሚያነብላቸውን አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ የአባይ ወንዝ **ድህረ ማዳመጥ** ከተነበበው ጽሀፍ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ፡፡ **ተገቢ** የቋንቋ አጠቃቀም ተጠቅመው ተፈጥሮን እንዲያደንቁ ማድረግ፡፡ በተሰጣቸው ርዕስ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ **ቅድመ ንባብ** የቀደመ እውቀታቸውን መሰረት	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ○ ለምሳሌ አባይ የት ይገኛል ➢ ስለተፈጥሮ መጠየቅ ○ ለምሳሌ አስኪ የአባይን ጥቅም ግለጹ ➢ የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላትን ለይተው አንዲወያዩባቸው ማድረግ ➢ የአንቀጹን ሃይለቃል አንዲያወጡ ማድረግ ➢ ለተለመዱ ቃላት ብያኔ አንዲሰጡ ማድረግ ➢ ስለቋንቋው መሰረታዊ መወቅር

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃመሳሪያዎች	ምዘና
ይመሰርታሉ፡፡ ➢ ለተለመዷዊ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ ➢ የመጀመሪያ ቋንቋን መሰረታዊ መዋቅር ይለያሉ፡፡		ያደረጉጥያቄዎችበመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ ለምሳሌ ስለተፈጥሮ ምንታውቃላችሁ **በለሆሳስያ** ንባብ በትክክል እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ጥያቄ መጠየቅ **ድህረ ንባብ** ምንባቡን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ሰእል ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ የቀረበላቸውን ስእል መሰረትአድርገውአንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ ለተለምዷዊ ቃላት ብያኔ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡ መሰረታዊ የቋንቋ መዋቅርን በተመለከተ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡	መጠየቅ

ምዕራፍ ሁለት የቤተሰብ እቅድ (9 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቅውጤት

ከዚህ የምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በጥሞና ያዳምጣሉ፡፡
- በቤተሰብ እቅድ ምንነት ላይ ይወያያሉ፡፡
- ቀላል ሁነቶችን ይተርካሉ፡፡
- የቤተሰብ እቅድን መሰረት አድርገው በሚሰጡ አስተያየቶች ላይ ይከራከራሉ፡፡
- ስዕሎችን ያነባሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡- • ጽሁፉን በአትኩሮት ያዳምጣሉ፡፡ • ቀላል ሁነቶችን በቅደም ተከተል ይተርካሉ፡፡ • አንብበው ስአሎችን ይገልጻሉ፡፡ • በ ሶስት አንቀጽ ኢመደበኛ ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡ • አዳዲስ ቃላትን ለይተው ትርጉም ይሰጣሉ፡፡ • የንቋውን መሰረታዊ መወቅር ጠብቀው አረፍተ ነገር	• ማዳመጥ • መናገር • ማንበብ • መጻፍ • ቃላት • ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-የኋላ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ ምሳሌ ስለቤተሰብ ምን ታውቃላችሁ **በማዳመጥ ጊዜ** ፡-እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ፡፡ ምሳሌ ቤተሰብ **ድህረ ማዳመጥ**፡- ካዳመጡት ውስጥ የወጡ ጥቂዎችን መጠየቅ ቀላል ሁነቶችን በቅደም ተከተል አንዲተርኩ ማድረግ ስለ ቤተሰብ አቅድ እንዲወያዩ ማድረግ ስለርአሱ የተለየዩ ጥያቄዎች መጠየቅ ቅድመ ንባብ የቀደመ እውቀትን በመጠየቅ	• ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ምሳሌ፡, የቤተሰብ እቅድ ምን ማለት ነው • የቤተሰብ አቅድን አሰፈላጊነት መጠየቅ • የምንባቡን ዋና ሃሳብ እንዲያጠቃልሉ መጠየቅ • የያንዳንዱን አንቀጽ ሀይለቃል አንዲያወጡ መጠየቅ • የተወሰኑ አዳዲስ ቃላትን አንዲገልጹ መጠየቅ • የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅር

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ይመሰርታሉ፡፡		ማነቃቃት ምሳሌ ስለቤተሰብ አቅድ ምን ታውቃለችሁ የንባብ ጊዜ ስዕሉን አይተው እንዲገልጹ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ ድህረ ንባብ ምንባቡን መሰረት አድርገው ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ (ስዕል ያስፈልጋል) መረጃ ሰብስበው ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ በሶስት አንቀጽ አስረጅ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ጽሁፋቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተራረሙ ማድረግ ከቀረበላቸው ጽሁፍ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ ቋንቋን መሰረታዊ መዋቅር ጠብቀው ዓ. ነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ	አንዲገልጹ መጠየቅ

ምዕራፍ ሶስት በጎፍቃደኝነት (9 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህ የትምህርት ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ያደመጡትን ያንጸባርቃሉ፡፡
- ስለበጎ ፍቃደኝነት ይገልጻሉ፡፡
- የጽሁፉን ዋና ሀሳብ መልሰው ይገልጻሉ ፡፡
- በጎ ፍቃደኞች በምን በምን ዙሪያ እንደተሰማሩ ይለያሉ ፡፡
- ከጽሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ያወጣሉ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህረት በኋላ ፡- ➢ ያደመጡትን መልሰው ያንጸባርቃሉ ፡፡ ➢ ከጓደኞቻቸው ጋር ምልልስ ያካሂዳሉ ፡፡ ➢ አንብበው የጽሁፉን ዋና መልዕክት እንደገና ይገልጻሉ፡፡ ➢ ካነበቡት ውስጥ ተዘውታሪ ቃላት ያወጣሉ፡፡ ➢ አራት አንቀጽ ያለው	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋስው	**ቅድመ ማዳመጥ፡-የኋላ** እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ ምሳሌ በጎፍቃደኝነት ምንድነው **በማዳመጥ ጊዜ** አጫጭር ንግግር በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ እና ሌሎች አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ምሳሌ መረዳት **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የሚሰሯቸው ስራዎች መስጠት ስለመረዳዳት እንዲገልጹ ማድረግ ስለ መረዳዳት አጭር ምልልስ እንዲያቀርቡ	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ➢ ምሳሌ የመረዳዳት አስፈላጊነት ምንድነው ➢ እርስ በእርስ መረዳዳት ያለውን ጥቅም እንዲገልጹ ማድረግ ➢ የምንባቡን ዋና ሃሳብ እንዲያጠቃልሉ ማድረግ ➢ በምንባብ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ ➢ ከአንቀጽ ውስጥ ሀይለ ቃል እንዲያወጡ ማድረግ ➢ ለድርብ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ቀስቃሽ ጽሁፍ ይጽፋሉ ። ➢ ለድርብ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ ። ➢ የቃላትን ነጠላ እና ብዙ ቁጥር ቅርጽ ይለያሉ		ማድረግ **ቅድመ ንባብ** ቁልፍ ቃላትን ከምንባቡ እንዲያወጡ ማደርግ ምሳሌ በጎፍቃደኝነት **የንባብ ጊዜ** ምንባቡን አንብበው ዋናውን ሀሳብ እንደገና እንዲገልጹ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ **ድህረ ንባብ** ምንባቡን መሰርት አድርገው ጽሁፋዊ ስራዎችን እንዲጽፉ ማድረግ (የቃላት ሰንጠረዥ ያስፈልጋል) በሶስት አንቀጽ አሳማኝ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ (በጎ ፍቃደኝነት) ጽሁፋቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተራረሙ ማድረግ ለድርብ ቃላት ብያኔ እንዲሰጡ ማድረግ የነጠላ እና ብዙ ቁጥር ቅርጾችን እንዲለዩ ማድረግ	ማድረግ ➢ ስለብዙ እና ነጠላ ቁጥር ቅርጾች መጠየቅ

ምዕራፍ አራት የታዋቂ ሰዎች የህይወት ታሪክ (12 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቅውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በማዳመጥ ያብራራሉ ።
- የህይወት ታሪክን ምንነት ይገልጻሉ።
- ከጽሁፉ ውስጥ የምክንያት እና የውጤት ግንኙነትን ይለያሉ ።
- የታዋቂ ሰው የህይወት ታሪክ ይጽፋሉ ።

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡- ➢ አዳምጠው የጽሁፉን ሀሳብ ያደንቃሉ ። ➢ መመሪያዎቹን በተመለከተ በቡድን ይወያያሉ ። ➢ ተዘውታሪ ፊሊጣዊ አነጋገሮችን ይገልጻሉ ። ➢ አያያዥ ቃላትን ይለያሉ ➢ የተለመዱ ቃላትን ለተለያዩ አላማ ይጠቀማሉ ። ➢ ሀረግን ይገልጻሉ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-የኋላ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት።። ምሳሌ ስለ ህይወት ታሪክ ምን ታውቃላችሁ **በማዳመጥ ጊዜ** አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ። ምሳሌ ታወቂ ሰው **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት አድርው የሚሰሯቸው ጥያቄዎች መስጠት የህይወት ታረክ አጻጻፍን እንዲለማመዱ ማድረግ መመሪያዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ ለህይወት ታሪክ እንዲለማመዱ ማድረግ **ቅድመ ንባብ** ስለፊሊጣዊ አነጋገሮች መጠየቅ	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ➢ ምሳሌ የህይወት ታሪክ ስንጽፍ የምንከተላቸው ቅደም ተከተላዊ መንገዶች ምንድናቸው ➢ ሰለአንድ ታዋቂ ሰው የህይወት ታሪክ እንዲናገሩ ማድረግ ➢ የምንባቡን ዋና ሃሳብ እንዲያጠቃልሉ ማድረግ ➢ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ የምንከተላቸውን ቅደም ተከተሎች እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ስማዊ ሀረግ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ የተለመዱ ቃላትን ተጠቅመው

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
		ምሳሌ ከፈረሱ ጋሪው **የንባብ ጊዜ** ምንባቡን አንብበው ዋናውን ሀሳብ እንደገና አንዲገልጹ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ **ድህረ ንባብ** ምንባቡን መሰርት አድርገው ጽሁፋዊ ስራዎችን እንዲጽፉ ማድረግ የተለመዱ ፊሊጣዊ አነጋገሮችን እንዲናገሩ ማድረግ (የህይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያ ያስፈልጋል) መሸጋገሪያ ቃላትን እንዲጽፉ ማድረግ በመሸጋገሪያ ቃላት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ ሀሳባቸውን ለመግለጽ የተለመዱ ቃላትን እንዲጠቀሙ ማድረግ ከዓ.ነሮች ውስጥ ሀረጎችን እንዲለዩ ማድረግ	ስሜታቸውን እንዲያንጸባርቁ ማድረግ ➢ ስለስማዊ ሀረግ መጠየቅ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ አምስት ውሃናጥቅሙ (9 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህ ምዕራፍትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ከሚደመጡ ንግግሮች ውስጥ ማስታወሻ ይይዛሉ ።
- ስለውሃ ጥቅም ይገልጻሉ።
- የራሳቸውን ዝንባሌ እና ፍላጎት ይገልጻሉ ።
- በርካታ ቃላትን ይዘረዝራሉ ።
- የውሃ አይነቶችን ይዘረዝራሉ ።

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡- ➢ የጽሁፉን ይዘት ይገነዘባሉ ➢ ቀላል መረጃዎችን ይጠይቃሉ ➢ የምክንያት እና ወጤት ግንኙነትን ይለያሉ ። ➢ ጽሁፍ ይተርካሉ ። ➢ የቃላትን ፍካሪያዊ ፍቺ በመለየት ትርጉም ይሰጣሉ ➢ ገቢርና ተገቢሮዓ. ነገርን ይዘረዝራሉ ።	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-የኋላ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት።። ምሳሌ የውሃ ጥቅም ምንድነው **በማዳመጥ ጊዜ** አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ። ምሳሌ ውሃን በአግባቡ መጠቀም **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የሚሰሯቸው ስራዎች መስጠት ስለ ውሃ አይነቶች መረጃ ሰብስበው እንዲወያዩ ማድረግ (የሚጠጣ እና የማይጠጣ) **ቅድመ ንባብ** ስለምክንያት እና ውጤት ግንኙነት	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ○ ምሳሌ የውሃ አይነቶችን ዘርዝሩ ➢ ውሀን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንዳለባቸው መረጃዎችን እንዲሰበስቡ ማድረግ ➢ ከምንባቡ ውስጥ የውሃ አያያዝ ዘዴን እንዲገልጹ ማድረግ ➢ አንድ ተራኪ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
		መጠየቅ **የንባብ ጊዜ** ምንባቡን አንብበው የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት እንዲለዩ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ ድህረ ንባብ ምንባቡን መሰርት አድርገው ምክንያት እና ውጤትን የተመለከቱ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ተራኪ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር ጽሁፍ እንዲያስተካክሉ ማድረግ የቃላትን እማሬያዊ ፍቺ በተመለከተ እንዲያብራሩ ማድረግ ገቢርና ተገቢሮ ዓ. ነገሮችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ	➢ ለተወሰኑ ቃላት እማሬያዊ ፍቺዎቻቸውን አንዲገለጹ ማድረግ ➢ የተለመዱ ቃላትን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ገቢርና ተገቢሮ ዓ. ነገሮችን ልዩት እንዲገልጹ ማድረግ

አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ሰባተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ ስድስት፡- የሰዎች ዝውውር (9 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቀው ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ካዳመጡት ነገር በመነሳት ዋናውን ሀሳብ ይገልጻሉ፡፡
- የሰዎችን ዝውውር ጽንሰሃሳብ ይገልጻሉ፡፡
- ከጓደኞቻቸው ጋር በራስ በመተማመን ይናገራሉ፡፡
- በትክክል ያነባሉ፡፡
- የሰዎች ዝውውር የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ይገልጻሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡- ➢ ያዳመጡትን ተገንዝበው ይተነትናሉ ፡፡ ➢ በራስ በመተማመን ይናገራሉ ➢ የተሰጠውን ጽሁፍ በትክክል ያነባሉ ፡፡ ➢ የገላጭ ጽሁፍን መዋቅር ያብራራሉ ➢ የቃላትን እማሪያዊ ፍቺ ይገልጻሉ ➢ የዓ.ነገር አይነቶችን ከአገልግሎታቸው አንጻር	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-የኋላ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ ምሳሌ የሰዎች ዝውውር ምንድነው **በማዳመጥ ጊዜ** አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ ፡፡ ምሳሌ የሰዎች ዝውውር ስጋት **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት አድርው የሚሰሯቸው ስራዎች መስጠት ስለ ሰዎች ዝውውር ጠንካራ እና ደካማ ጎን እንዲወያዩ ማድረግ ቅድመ ንባብ ስለርዕሱ መጠየቅ (ስለ ሰዎች ዝውውር ምንታውቃላችሁ)	• ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ምሳሌ የሰዎች ዝውውር የሚያደርሱት ተጽዕኖ ምንድናቸው • ስለሰዎች ዝውውር ጉዳት መጠየቅ • የምንባቡን የተለያዩ ክፍሎች መጠየቅ • የሰዎች ዝውውርን የተመለከቱ ገላጭ ጽሁፎች እንዲጽፉ ማድርግ • ለተወሰኑ ቃላት ፍካሪያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ • ስለተተግባሪ ዓ. ነገሮች መጠየቅ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ይገልጻሉ		የንባብ ጊዜ ምንባቡን በትክክል እንዲያነቡ ማድረግ (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ) **ድህረ ንባብ** ትክክለኛ አነባበብ እንዲለማመመዱ ማድረግ (ስዕል ያስፈልጋል) የገላጭ ጽሁፍን ቅርጽ ተገንዝበው እንዲወያዩ እና እንዲጽፉ ማድረግ የቃላትን ፍካሪያዊ ፍቺ እንዲገልጹ ማድረግ የዓ. ነገር አይነቶችን ከአገልግሎታቸው አንጻር እንዲለዩ ማድረግ	

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍሰባት፡- ማህበራዊ ግንኙነት (12 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በጥልቀት ያዳምጣሉ ::
- የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነትን ይገልጻሉ::
- በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ጽሁፍ ይጽፋሉ ::
- ድብልቅ ዓ.ነገር ይመሰርታሉ ::

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡- ➢ መረጃ ሰጪ ጽሁፎችን በጥልቀት ያዳምጣሉ :: ➢ በተወሰኑ ርዕሶች ዙሪያ ከጓደኞቻቸው ጋር ይስማማሉ :: ➢ የተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ይጠቀማሉ :: ➢ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ጽሁፍ ይጽፋሉ ➢ የቃላትን ተመሳሳይ ያዛምዳሉ ➢ ተተግባሪ ዓ.ገርይመሰርታሉ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-የቀደመ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት:: ምሳሌ ማህበራዊ ግንኙነት ምንድነው **በማዳመጥ ጊዜ** አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ :: ምሳሌ ማህበራዊነት **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት አድርው የሚሰሯቸው ስራዎች መስጠት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲስማሙ ማድረግ ምሳሌ የማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊነት **ቅድመ ንባብ** ስለ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ጥቅም መጠየቅ **የንባብ ጊዜ** በፈሊጣዊ አነጋገሮች ላይ ተመስርቶ	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ምሳሌ የማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊነት ምንድነው ➢ የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት በተመለከተ ተወያይተው እንዲስማሙ ማድረግ ➢ የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት በተመለከተ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ተጠቅመው እንዲያጠቃልሉ ማድርግ ➢ ማህበራዊ ግንኙነትን የተመለከተ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ የቃላትን ተመሳሳይ እንዲያዛምዱ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
		የቀረበውን ጥያቄ እንዲያነቡ ማድረግ (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ) **ድህረ ንባብ** ፈሊጣዊ አነጋገርን በተመለከተ ያነበቡትን ምንባብ ተገንዝበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ (ስዕል ያስፈልጋል በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት አካተው ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ የቃላትን ተመሳሳይ እንዲያዛምዱ ማድረግ ተግባራዊ ዓ. ነገሮች እንዲመሰርቱ ማድረግ	➢ የተተግባሪ ዓ. ነገሮችን የተለያዩ ክፍሎች እንዲገልጹ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ ስምንት፡- ሱስ (9 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- አዳምጠው ተመሳሳይ ጽሁፍ ይጽፋሉ ::
- ሱስ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ይገልጻሉ ::
- የጽሁፉን ዋና ሀሳብ በተመከተ ዘገባ ያቀርባሉ ::
- አድማጩን መርዳት ይቻል ዘንድ ጽሁፍን እንደገና ይከልሳሉ ::

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡- ➢ ተመሳሳይ ጽሁፍ ይጽፋሉ ➢ ሀሳብ እንደገና ያዋቅራሉ ➢ የጹፉን ዋና መልዕክት በቃል ይናገራሉ :: ➢ በጽሁፍ ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ ➢ የተለመዱ ቃላትንአውዳዊ ፍቺ ይገልጻሉ ውስብስብ የዓ. ነገር ይመሰርታሉ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-የቀደመ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ ምሳሌ ሱስ ምንድነው **በማዳመጥ ጊዜ** አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ :: ምሳሌ ሲ.ጋራ ማጨስ **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት አድርው ተመሳሳይ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ሀሳብን እንደገና በማዋቀር እንዲናገሩ ማድረግ (የሲ.ጋራ ማጨስ ተጽዕኖ) (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ) ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው ጽሁፍ ባግባቡ እንዲጽፉ ማለማመድ ለተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ ውስብስብ አረፍተ ነገር አንዲመሰርቱ ማድረግ	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ምሳሌ ሱስ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምንድነው ➢ ሀሳባቸውን እንደገና አንዲያዋቅሩ መጠየቅ ➢ ሱስ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በቃል አንዲያቀርቡ መጠየቅ ➢ ስርዐተ ነጥቦችን እንዴት አንደሚጠቀሙ መጠየቅ ➢ ለተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ መጠየቅ ➢ ድርብ ዓ. ነገሮችን እንዲያርሙ መጠየቅ

ምዕራፍ ዘጠኝ፡-የአገር ፍቅር (12 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቅውጤት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- አዳምጠው የጽሁፉን ጽንሰሃሳብ ከህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ ::
- የሀገር ፍቅርን ምንነት ይገልጻሉ ::
- ለተወሰነ አላማ ያነባሉ ::
- የሀገር ፍቅርን ያደንቃሉ ::

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡- ➢ ጽሁፉንአንብበው ከራሳቸው ህይወት ጋር ያዛምዳሉ ➢ በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ተወያይተው ከስምምነት ላይ ይደርሳሉ :: ➢ ለተወሰነ አላማ ያነባሉ :: ➢ የሥዕሉን መልዕክት በጽሁፍ ይገልጻሉ ➢ ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይገልጻሉ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋስው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-የቀደም እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ ምሳሌ የሀገር ፍቅር ምንድነው **በማዳመጥ ጊዜ** አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ :: ምሳሌ የአደዋ ድል **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት አድርው ከራሳቸው ጋር ማዛመድ የአገር ፍቅርን አስፈላጊነት በተመለከተ ተወያይተው በሃሳቡ ላይ ከስምምነት እንዲደርሱ ማድረግ **ቅድመ ንባብ** ስለ ርዕሱ መጠየቅ ሰለአሀገር ፍቅር ምን ታውቃላችሁ	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ምሳሌ የአር ፍቅር ውጤቱ ምንደንው ➢ ስለአገር ፍቅር ተወያይተው እንዲስማሙ ማድረግ (የአድዋ ድል) ➢ ጽሁፉን በጥልቅ እንዲያነቡ ማድረግ ➢ ስለአገር ፍቅር ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
➢ ውስብስብ ዓ. ነገር ይመሰርታሉ		የንባብ ጊዜ ለተወሰኑ አላማዎች ምንባብ እንዲያነቡ ማድረግ (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ) ድህረ ንባብ ምንቡን ተገንዝበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ (ስዕል ያስፈልጋል) አድዋን በተመለከተ የተሳሉ ስዕሎችን ጽሁፍ እንዲገልጹ ማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር የተገለጸውን ጽሁፍ ማረም ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት የቋንቋውን ህግ ጠብቆ ውስብስብ ዓ.ነገር መመስረት	➢ ውስብስብ ዓ. ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ አስር፡- ቃላዊግጥም (12 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ጽሁፉን አዳምጠው ይተረጉማሉ ::
- ለቃል ስነ-ግጥም ብያኔ ይሰጣሉ ::
- የቃል ግጥም አይነቶችን ያብራራሉ ::
- ዜማውን ጠብቀው ግጥም ያነባሉ ::

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡- ➢ ጽሁፉ አንብበው ይተረጉማሉ :: ➢ ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥም ይናገራሉ :: ➢ ዜማውን ጠብቀው ግጥም ያነባሉ :: ➢ ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥም ይጽፋሉ ➢ ዘይቢያዊ ቃላትን ያብራራሉ ➢ በጽሁፍ ውስጥ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-የቀደመ እወቀታቸውን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ ምሳሌ ቃላዊ ግጥም ምንድነው **በማዳመጥ ጊዜ** አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ :: ምሳሌ አጭር ግጥም **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያካዳመጡትን መሰረት አድርው ከራሳቸው ጋር ማዛመድ አዳምጠው ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥም እንዲናገሩ ማድረግ **ቅድመ ንባብ** ስለርዕሱ መጠየቅ ስለ ቃላዊ ግጥም ምን ታውቃላችሁ **የንባብ ጊዜ** ተገቢውን አገላለጽ ተጠቅመው ምንባቡን አንዲያነቡ ማድረግ (በመሃል ጥያቄ መጠየቅ)	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ምሳሌ የቃላዊ ግጥም መልዕክት ምንድነው ➢ ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥም አንዲናገሩ ማድረግ ➢ ቃላዊ ግጥም እንዲያነቡ ማድረግ ➢ ቃላዊ ግጥም እንዲጽፉ ማድረግ ➢ የዘይቤአዊ አባባሎችን ትርጉም አንዲያብራሩ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መረጃ መሳሪያዎች	ምዘና
አያያገሮችን ይጠቀማሉ		ድህረ ንባብ ምንባቡን ተገንዝበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ (ተጨማሪ ቃላዊ ግጥም ያስፈልጋል) ተመሳሳይ ቃላዊ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር የቃላዊ ግጥምን ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱ ማድረግ ዘይቤያዊ አገላላጾችን እንዲያብራሩ መጠየቅ	

አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ስምንተኛ ክፍል አንደኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ አንድ፡ የሥራ ሥነ- ምግባር (9) ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- በአትኩረት አድምጠው ይመልሳሉ፡፡
- የሥራ ስነ- ምግባርን ጽንሰ ሀሳብ ይገልጻሉ ፡፡
- አዳዲስ ሀሳቦችን አካተው ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡
- የስራ ስነ ምግባር አመላካች ነገሮችን ይገልጻሉ፡፡
- የመጀመሪያ ቋንቋን ትክክለኛ የሰዋሰው አወቃቀር ይጠቀማሉ ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃመሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ በጥሞና አዳምጠው በተነገረበት አውድ መሰረት ይመልሳሉ ➢ ቋንቋን በተለያ ሁነቶች ውስጥ ይጠቀማሉ ➢ አጠቃላይ ጭብጡን ለመረዳት በለሆሳስ ያነባሉ ➢ አዲስ ሀሳብ አካተው ጽሁፍ ይጽፋሉ ➢ ተዘውታሪ ቃላትን በተለያ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡-ተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ ለምሳሌ ፡- **የስራ ስነ- ምግባር ምንድነው ?** **የማዳመጥ ጊዜ**፡-መምህሩ የሚያነብላቸውን አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡- ጠንካራ የስራ ባህል **ድህረ ማዳመጥ** ባዳመጡት መሰረት ትክክለኛ መልስ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡ በተለያዩ አውዶች ውስጥ ቋንቋውን በመጠቀም እንዲወያዩ ማድረግ (የስራ ስነምግባር፣ ጠንካራ የስራ ባህል) **ቅድመ ንባብ**፡- ተማሪዎችን ስለርዕሱ መጠየቅ	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ➢ ለምሳሌ ጠንካራ ሰራተኝነት ምንድነው? ➢ ስልጠንካራ ሰራተኛ ምንነት ነጥብ በነጥብ መጠየቅ ➢ የሞያ ስነ- ምግባርን በተመለከተ አጠቃላይ ሀሳብን የያዘ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ተዘውታሪ ቃላትን በተለያዩ አውድ ውስጥ እንዲጠቀሙ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃመሳሪያዎች	ምዘና
አውዶች ይጠቀማሉ ➢ የቋንቋውን ተገቢ መዋቅር ጠብቀው ድርሰት ይጽፋሉ		ለምሳሌ፡-ስለስራ ስነ-ምግባር ምን ታውቃላችሁ ? **በንባብ ጊዜ፡-** አጠቃላይ ጭብጡን ለማግኘት ይቻል ዘንድ በለሆሳስ እንዲያነቡ በማድረግ ፤ የተማሪዎችን የአቅም ደረጃ የጠበቀ ጥያቄ በመሀል ላይ መጠየቅ ። **ድህረንባብ፡-** በምንባቡ አጠቃላይ ሀሳብ መሰረት የተሰጣቸውን ጥያቄ እንዲሰሩ ማድረግ ። የስራ ስነ- ምግበርን በተመለከተ የራሳቸውን ሀሳብ ጨምረው እንዲጽፉ ማደርግ። ተዘውታሪ ቃላትን በተለያየ አውድ ውስጥ እንዲጠቀሙ ማድረግ። የቋንቋውን ተገቢ መዋቅር ጠብቀው ድርሰት እንዲጽፉ ማድረግ።	ማድረግ

ምዕራፍ ሁለት ባህላዊ ቅርስ (12 ክፍለጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የሌሎችን ሀሳብ በአትኩሮት ያዳምጣሉ፡፡
- ከምንባቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- የባህላዊ ቅረስን ምነነት ያብራራሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ በበጥሞና የሌሎችን ሀሳብ እያዳመቱ ይመልሳሉ ➢ የተለያዩ ውስብስብ ሁነቶችን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ይተርካሉ ➢ ስዕሉን አንብበው መልዕክቱን በተመለከተ ዘገባ ያቀርባሉ ➢ በ3 አንቀጽ አከራካሪ ድርሰት ይጽፋሉ ➢ አዳዲስ ቃላትን በተለያዩ	• ማዳመጥ • መናገር • ማንበብ • መጻፍ • ቃላት • ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡- ተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ **ለምሳሌ ባህላዊ ቅረስ ምንድነው ?** የማዳመጥ ጊዜ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ በጥሞና አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡ የሶፉመር ዋሻ **ድህረ ማዳመጥ** የሌሎችን ሀሳብ በአትኩሮት አዳምጠው እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡ ውስብስብ ሁነቶችን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንዲተርኩ ማድረግ ፡፡ **ቅድመ ንባብ** ተማሪዎችን ስለርዕሱ መጠየቅ ለምሳሌ ስለባህላዊ ቅርስ ምን ታውቃላችሁ ? **በንባብ ጊዜ፡- በምንባብ ውስጥ ያለውን** የስዕል ሀሳብ ላይ	➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ ለምሳሌ ባላዊ ቅረስ ምን ማለት ነው ? ➢ ስለአንድ ባህላዊ ቅረስ እነዲተርኩ ማድረግ ➢ ስልቀረበላቸው የባህላዊ ቅርስ ስዕል ማጠቃለያ እንዲሰጡ ማድረግ ➢ ስለ ባህላዊ ቅርስ አከራካሪ ድርሰት እንዲጽፉማድረግ ➢ አዳዲስ ቃላትን በተለያ አውድ ውስጥ እንዴት እንደሚጠቀሙመጠየቅ ➢ ከዓ.ነገር ውስጥ የአሁን ጊዜን

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
አውድ ውስጥ ይጠቀማሉ		መልመጃዎችን በማዘጋጀት እንዲሰሩ ማድረግ፤ የተማሪዎችን የአቅም ደረጃ የጠበቀ ጥያቄ በመሀል ላይ መጠየቅ :: **ድህረ ንባብ፡-** ስዕሉን በተመለከተ አንብበው ስለምን እንደሚያነሳ መጠየቅ (ስዕል ያስፈልጋል) :: በሶስት አንቀጽ አከራካሪ ድርሰት እንዲጽፉ ማድረግ አዳዲስ ቃላትን በተለያየ አውድ ውስጥ እንዲጠቀሙ ማድረግ:: የቋንውን ተገቢ መዋቅር ጠብቀው እንዲጽፉ ማድረግ::	እንዲለዩ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ ሶስት፡- ሰባዊ እሴቶች (12) ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት፡-

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- አዳምጠው ጽሁፍን ይመዝናሉ፡፡
- ስለሰዎችን ማክበር ምንነት ያብራራሉ ፡፡
- ከሌሎች ጋር ምልልስ ያደርጋሉ ፡፡
- የሰባዊ እሴቶች አላባውያንን ይዘረዝራሉ ፡፡
- ባለአራት አንቀጽ ጽሁፍን ይመዝናሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው መልዕክቱን ይመዝናሉ ፡፡ ➢ ከሌሎች ጋር ምልልስ ያደርጋሉ ➢ የጽሁፉን ሀሳብ ከራሳቸው ጋር ያዋህዳሉ ➢ ከጽሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላት ያወጣሉ ➢ አራት አንቀጽ ያለው	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡- የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡ **ለምሳሌ፡-** ሰባዊ እሴት ማለት ምን ማለት ነው ? **የማዳመጥ ጊዜ** ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡- አክብሮት **ድህረ ማዳመጥ፡-** የማዳመጥ ተግባርን እያከናወኑ የሚያዳምጡትን ፅሁፍ እንዲገመግሙ ማድረግ፡፡ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስለሰባዊ እሴቶች ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ፡፡ **ቅድመ ንባብ** ተማሪዎችን ስለርዕሱ በመጠየቅ አንዲገምቱ ማድረግ	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ○ ለምሳሌ ሰባዊ እሴት ምን ማለት ነው ? ➢ ሰውን ማበር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲዘረዝሩ ማድረግ ➢ ከጽሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን እንዲያወጡ ማድረግ ➢ ቢያነስ ሶስት ሰውን ማክበሪያ ዘዴዎችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ ➢ የብዙቁጥር ቅርጾችን እንዲለዩ ማድረግ ○ እንዳለባቸው ጽሁፍ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
አመዛዛኝጽሁፍ ይጽፋሉ ➢ ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው ሀሳባቸውን ይገልጻሉ ➢ ነጠላ እና ብዙ ቁጥርን በትክክል ይጠቀማሉ፡፡		የንባብ ጊዜ ጸሁፉን መረዳት ይችሉ ዘንድ እንዲያነቡ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ ድህረ ንባብ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ተረድተው እንዲመልሱ ማድረግ (የቃላት ሰንጠረዥ ያስፈልጋል) ሰባዊ እሴትን በተመለከተ ባለ አራት አንቀጽ ፅሁፍ ይጽፋሉ:: ሀሳባቸውን ለመግለጽ ውስብስብ ቃላትን እንዲጠቀሙ ማድረግ:: ነጠላ እና ብዙ ቁጥር ቃላትን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡:	እነዲጽፉ ማድረግ ➢

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምርዕፍ አራት ፡ አጭር ልብ-ወለድ (12) ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪክ ይናገራሉ ።
- ስለአጭር ታሪክ ምንነት ይገልጻሉ ።
- በጽሁፍ ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ።
- የአጭር ልቦለድን አላባውያነ ይዘረዝራሉ።

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪክ ይናገራሉ ። ➢ እርስ በእረስ መመሪያ ይሰጣጣሉ ➢ አንብበው ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ይለያሉ ➢ በጽሁፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ ➢ ያልተለመዱ ቃላትን ለተለያ አላማ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡- ታሪክ በመንገር የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ ፡፡ **በማዳመጥጊዜ**፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ። ለምሳሌ አጭር ጽሁፍ **ድህረ ማዳመጥ፡ -የማዳመጥ ተግባሩን ካከናወኑ በኋላ** ተመሳሳይ ታሪኮችን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ አንድኛቸው ለሌላኛቸው መመሪያ እንዲሰጣጡ ማድረግ፡፡ **ቅድመ ንባብ**፡- ስለ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ምንነት ተማሪዎችን መጠየቅ፡፡ **በንባብ ጊዜ**፡- **ተማሪዎች ከምንባብ ውስጥ** አዳዲስ	➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ ለምሳሌ የአጭር ልቦለድ ክፍሎች ምንድናቸው? ➢ የአጭር ልቦለድ አላባውያንን እንዲገልጹ ማድረግ ➢ አዳዲስ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እንዲለዩ ማድረግ ➢ የሽግግር ቃላትን እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ያልተለመዱ ቃላትን ለተለያየ አላማ እንዲጠቀሙ ማድረግ ➢ ሀረግን ተጠቅመው ዓ .ነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ይጠቀማሉ ➢ ሀረጎችን በዓ. ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ		ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እንዲለዩ ማድረግ ፤ የተማሪዎችን የአቅም ደረጃ የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ ።። **ድህረ ንባብ፡-** አዳዲስ ፈሊጣዊ አንጋገሮችን ከምንባቡ ውስጥ እያወጡ ፈቺ አንዲሰጡ ማድረግ፡፡ (መዘገበ ቃላት ያስፈልጋል) በጽሁፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትን መጠቀም ።፡ ያልተለመዱ ቃላትን ለተለያዩ አላማ መጠቀም፡፡ ሀረግን ተጠቅሞ ዓ. ነገር መመስረት ።፡	➢

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ምዕራፍ አምስት፡የህዝብ ብዛት (9) ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- በአትኩሮት አዳምጠው ጽሁፍን ይገልጻሉ፡፡
- ስለህዝብ ብዛት ምንነት ይገልጻሉ ፡፡
- ተራኪ ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡
- የህዝብ ብዛት በኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረውን ተጸዕኖ ይተነትናሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ በጥሞና አዳምጠው ጽሁፍን ይመዝናሉ ፡፡ ➢ ውስብስብ መረጃዎችን ይጠይቃሉ ➢ በጥልቀት አንብበው ምክንያት እና ውጤት ትስስሮችን ይገልጻሉ ➢ ተራኪ ጽሁፍ ጽፈው ይመዝናሉ ➢ ሀሳባቸውን የቃላትን እማሪያዊ ፍቺ ተጠቅመው ይገልጻሉ ➢ ገቢርና ተገብሮ ዓ. ነገሮችን	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ፡-** ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ፡፡ ምሳሌ:-የህዝብ ብዛት ማለት ምን ማለት ነው ? **የማዳመጥ ጊዜ ፡-** መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡- የውልደት ምጣኔ **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን ጽሁፍ መልዕክት የመመዘን ተግባር እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡ ስለ ህዝብ ብዛት እና ጥልቀት ስላላቸው መረጃዎች እንዲወያዩ ማድረግ ፡፡ **ቅድመ ንባብ፡-** አዲስ ሀሳብ እንዲፈጥሩ ማድረግ **ምሳሌ፡- የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት** **የንባብ ጊዜ፡-** ከጽሁፍ ውስጥ በምክንያት እና	➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ ○ ለምሳሌ የውልደት ምጣኔ ምንድ ነው ? ➢ ከሌላ ሰዎች የተገኙ የተወሳሰቡ መረጃዎችን መጠየቅ ➢ የምክንያት እና ውጤት ግንኙነትን አንዲለዩ ማድረግ ➢ ተራኪ ድርሰት አንዲጽፉ እና እንዲለማመዱ ማድረግ ➢ እማሪያዊ ፍቺዎችን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ይጠቀማሉ		ውጤት የተሳሰሩ ጽሁፎችን ማውጣትየተማሪዎችን ደረጃ የሚመጥን ጥያቄ በመሀል መጠየቅ፡፡፡ **ድህረ ንባብ፡-** ምንባቡን አንብበው የምክንያት እና ውጤት ግንኙነትን እየተመለከቱ ጥያቄዎችን አንዲመልሱ ማድረግ (ስዕል ያስፈልጋል) ተራኪ ጽሁፍ እንዲለማመዱ እና እንዲመዘኑ ማድረግ፡፡ እማሬያዊ ቃላትን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡ ገቢርና ተገብሮ ሀሳቦችን ተጠቅመው ዓ. ነገር እንዲፅፉ ማድረግ፡፡	➢ ገቢርና ተገብሮ ሀሳቦችን እንዲለዩ ማድረግ

አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ስምንተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

ምዕራፍ ስድስት፡ በረሃማነት (9) ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- አዳምጠው ጽሁፍን በመተንትን ይገመግማሉ፡፡
- የበረሃማነት ምንነትን ይገልጻሉ ፡፡
- በትክክል አንብበው ጽጉፉን በአጭሩ ያቀርባሉ፡፡
- በረሃማነት እና የዐየር ንብረት ለውጥ የሚያሣድረውን ተጽዕኖ ይተነትናሉ ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው እየተነተኑ ይመዘናሉ ፡፡ ➢ የተሰጣቸውን ርዕስ መሰረት አድርገው በራሳቸው በመተማመመን ይናገራሉ ➢ የተሰጣቸውን ጽሁፍ በትክክል በማንበብ ማጠቃላያ ይሰጣሉ ➢ የገላጭ ጽሁፍን መዋቅር ይመዘናሉ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ ፡፡ ምሳሌ፡- በረሃማነት ምንድነው ? **በማዳመጥ ጊዜ** ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ የአፈር መሸርሸር **ድህረ ማዳመጥ**፡- ያዳመጡትን ጽሁፍ መልዕክት የመመዘን ተግባር እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡ • የበረሃማነትን ምንነት በተመለከተ ተወያይተው በራስ በመተማመን እንዲናገሩ ማድረግ ፡፡ **ቅድመ ንባብ**፡- የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ማነቃቃት	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ለምሳሌ የአፈር መሸርሸር ምክንያት ምንድነው ? ➢ የበረሃማነት ወጤቶች ምን ምን እንደሆኑ መጠየቅ ➢ ስለበረሃማነት የማጠቃለያ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ስለውልደት አንዳንድ ነጥቦች እንዲያነሱ ማድረግ ➢ የቃላትን ፍካሬያዊ ፍቺዎች ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
➢ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ፍካሬያዊ ፍቺ ይጠቀማሉ ➢ ተግባር ተኮር ዓ. ነገር ይጽፋሉ		**ምሳሌ** ስለበረሃነት ምን ታውቃላችሁ **በንባብ ጊዜ፡- ማንባቡን** በትክክል እንዲያነቡ በማድረግ የጽሁፉን መልዕክት ማጠቃለያ እንዲያቀርቡ ማድረግ፤ ተማሪዎችን በመሀል በመሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡ **ድህረ ንባብ፡-** ምንባቡን አንብበው በማጠቃላያ ሀሳቦች ላይ የተነሱ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ (ስዕል ያስፈልጋል) የገላጭ ጽሁፍን መዋቅር መመዘንን እንዲለማመዱ ማድረግ ፡፡ እማሬያዊ ቃላትን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡ ተግባር ተኮር ዓ. ነገር እንዲመስርቱ ማድረግ	➢ ተግባር ተኮር ዓ. ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ

ምዕራፍ ሰባት፡ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ(9) ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- መረጃ ሰጭ ጽሁፍን በጥልቀት አዳምጠው ጽሁፍን ተግባራዊ ያድርጋሉ ።
- የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነት እና ሚያስከትለውን ውጤት ይገልጻሉ ።
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ።
- የዓ. ነገሮችን ተግባር እያወዳደሩ ያነጻጽራሉ ።

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ መረጃ ሰጪ ጽሁፉን አንብበው ተግባራዊ ያደርጋሉ ። ➢ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ይስማማሉ ➢ ያልተለመዱ ፊሊጣዊ አነጋገሮችን አንብበው ይጠቀማሉ ➢ በተለያዩ ርዕሶች ላይ የክፍል ደረጃውን ያማከለ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ።።። **ምሳሌ** ፡- የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምንድነው ? በማዳመጥ ጊዜ ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ። **ለምሳሌ**፡- የህጻናት መብት **ድህረ ማዳመጥ**፡- ከአዳመጡት ጽሁፍ ውስጥ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲተቹ ማድረግ ። ስለህጻናት መብት ተወያይተው ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። **ቅድመ ንባብ**፡- የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ማነቃቃት።።	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ➢ ለምሳሌ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምንድነው ? ➢ ስለ ህጻናት መብት እንዲገልጹ ማድረግ ➢ ፊሊጣዊ አገላለጾችን እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ስለጎጂናት መብት እንዲገልጹ ማድረግ ➢ የቃላትን ተቃራኒ እንዲያዛምዱ ማድረግ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ጽሁፍ ይጽፋሉ • ለቃላት ተቃራኒ ፍቺይሰጣሉ • ተግባር ዓ. ነገሮችን እያወዳደሩ ያነጻጽራሉ		**ምሳሌ፡-**ስለሀጻናትጉልበት ብዝበዛ ምንታውቃላችሁ? **የንባብ ጊዜ፡-** በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ ተማሪዎችን በማሀል በማሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡ **ድህረ ንባብ፡-** ያልተለመዱ ፊሊጣዊ አነጋገሮችን ከምንባቡ ውስጥ በመፈለግ እንዲገልጹ ማድረግ ፡፡ (የቃላት ሰንጠረዥ እና ስዕል ያስፈልጋል) የክፍል ደረጃውን ያማከለ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ቃላትን ከተቃራኒያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግየ ዓ. ነገርሮችን እንዲያወዳድሩ እና እንዲያነጻጽሩ ማድረግ፡፡	➢ የ ዓ. ነገሮችን ተግባር እንዲገልጹ ማድረግ

ምዕራፍ ስምንት፡ ሰላም (9) ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ጽሁፍን አንብበው ይተነትናሉ፡፡
- የሰላምን አስፈላጊነት ይገልጻሉ ፡፡
- የጽሁፉን ዋና ሀሳብ ያጠቃልላሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ስርዐተ ነጥቦችን በአግባቡ ይጠቀማሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው ጽሁፉን ይተነትናሉ ፡፡ ➢ ሀሳቡን እነደገና በማዋቀር ለአድማጮች ግልጽ እንዲሆንላቸው ያደርጋሉ ➢ አንብበው የጽሁፉን ዋና መልዕክት በማጠቃለል ያቀርባሉ ➢ በጽሁፍ ውስጥ ተገቢውን ስርዐተ ነጥብ ይጠቀማሉ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ፡፡ **ምሳሌ** ፡- ሰላም ምንድን ነው ? **በማዳመጥ ጊዜ** ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ ፡- የሰላም መኖር ለእድግት ያለው አስተዋጽኦ **ድህረ ማዳመጥ**፡- የአዳመጡትን ጽሁፍ ተገንዝበው ከውስጥ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡ ያዳመጡትን የጽሁፉን ሀሳብ ግልፅ በሆነ መንገድ እንደገና እንዲያዋቅሩ ማድረግ፡፡ **ቅድመ ንባብ** የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ማነቃቃት ፡፡	➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ለምሳሌ የሰላም መኖር ለእድገት ያለው አስተዋጽዖ ምንድነው ? ➢ የሠላምን ምንነት እንዲገልጹ ማድረግ ➢ ስለሰላም የማጠቃለያ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ስለሰላም ጥቂት ነጥቦች እንዲጽፉ ማድረግ ➢ የተለመዱ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ እንዲያብራሩ ማድረግ ➢ የውስብስብ ዓ. ነገሮችን የተለያዩ

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
➢ ለተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ ➢ ውስብስብ ዓ. ነገሮችን ይመሰርታሉ		**ምሳሌ ፡-** ስለሰላም ምን ታውቃላችሁ **ንባብ ጊዜ፡-** በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ ተማሪዎችን በመሀል በመሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡ **ድህረ ንባብ፡-**የምንባቡን ዋና ሀሳብ በማጠቃለል እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ (የስረዐተ ነጥብ ሰንጠረዥ ያስፈልጋል) የሥረዓተ ነጥብ ምልክቶችን በፅኑፍ ውስጥ በትክክለኛው ቦታ በማስገባት እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡ ውስብስብ ዓ. ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡	ክፍሎች እንዲለዩ ማድረግ

ምዕራፍ ዘጠኝ፡ የአየር ንብረት (9) (ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የጽሁፍን ሀሳብ አዳምጠው ይገመግማሉ፡፡
- ስለ አየር ንብረት ምንነት ያብራራሉ ፡፡
- ለተለያየ አላማ ያነባሉ፡፡
- የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ውጤት ያብራራሉ፡፡

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ አዳምጠው ጽሁፉን ይመዘናሉ ፡፡ ➢ በተሰጣቸው ርእስ በክፍል ውስጥ ይስማማመሉ ➢ ለተለያየ አላማ ያነባሉ ➢ ጽሁፉን ተመልክተው ጥልቅ ገለጻ ያካሂዳሉ ➢ ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ ➢ ድርብ ድብልቅ ዓ. ነገሮችን ይመሰርታሉ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	• **ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ ፡፡ ምሳሌ ፡- የአር ንብረት ምንድነው ? • በማዳመጥ ጊዜ ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡- የአየር ንብረት **ድህረ ማዳመጥ** መልዕክቱን የተመለከቱ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡ • በተሰጠው ርዕስ ላይ በክፍል ውስጥ ተወያይተው ስምምነት ላይ መድረስ /የአየር ንብረት ለውጥ በሚል ርእስ ይከራከራሉ፡፡ **ቅድመ ንባብ**፡- የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ማነቃቃት	➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ ➢ ለምሳሌ የአየር ንብረት ለውጥ ምንድነው ? ➢ የአየር ንብረትን ለመከላከል መፍትሄው ምን እነደሆነ መጠየቅ ➢ ስለአየር ንብረት የማጠቃለያ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ከስዕል የተገነዘቡትን ዘርዝረው እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ያልተለመዱ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ እንዲያብራሩ ማድረግ ➢ ውስብስብ ዓ. ነገሮች ምንነት

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
		ምሳሌስለአየር ንብረት ለውጥ ምን የምታውቁትነገር አለ **የንባብ ጊዜ፡-** በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ ተማሪዎችን በመሀል በመሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡ **ድህረ ንባብ፡-** ምንባቡን አንብበው ከምንባብ የወጡ የተለያዩ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ (ስዕል ያስፈልጋል) ስዕልን ተመልክተው ጥልቅ ትንታኔ እንዲሰጡ ማለማመድ፡፡ ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት፡፡ ውስብስብ ዓ. ነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ ፡፡	መጠየቅ

ምዕራፍ አስር፡ ተውኔት (12) (ክፍለ ጊዜ)

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የጽሁፍን ሀሳብ አዳምጠው ይተነትናሉ።
- ስለ ተውኔት ምንነት ትንታኔ ይሠጣሉ ።
- የተውኔት አላባውያንን ይዘረዝራሉ።
- የጽሁፉ ውስጥ የተለያዩ አያያዞችን ይጠቀማሉ።

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- ➢ ለጽሁፉ ተንታኔ ይሰጣሉ ። ➢ ጽሁፉን ይተርካሉ ➢ ጽሁፉን አንብበው ➢ የትወናው አካል ይሆናሉ ➢ ተመሳሳይ የተውኔት ጽሁፍ ያዘጋጃሉ ➢ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ዘይቤ ይጠቀማሉ ➢ በጽሁፍ ውስጥ	➢ ማዳመጥ ➢ መናገር ➢ ማንበብ ➢ መጻፍ ➢ ቃላት ➢ ሰዋሰው	**ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ። ምሳሌ ፤ ተውኔት ምንድነው ? በማዳመጥ ጊዜ ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ። ለምሳሌ፡- አጫጭር ጨውውት **ድህረ ማዳመጥ**፡- ያዳመጡትን ፅሁፍ መልዕክት ከተረዱ በኋላ ከውሱ የወጡ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ ። ጽሁፉን እንዲተርኩ ማድረግ **ቅድመ ንባብ** ፡-የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት በጥያቄ መቀስቀስ ተውኔት ምንድነው **የንባብ ጊዜ**፡- በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ።	➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ ለምሳሌ የተውኔት አይነቶች ምን ምንናቸው ? ➢ ጥያቄዎችን እንዲመልስ ማድረግ ➢ የተወሰኑ የተውኔት ክፍሎችን እንዲተርኩ ማድረግ ➢ የተውኔት አይነቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ ➢ የተውኔቱን ጭብጥ እንዲጽፉ ማድረግ ➢ ሀሳባቸውን እንዴት በዘይቤ አገላላጽ እንደሚጽፉ መጠየቅ ➢ አያያገሮችን እንዴት

የአማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ

ብቃት	ይዘት	የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች	ምዘና
የተለያዩ አያያገሮችን ይጠቀማሉ		ተማሪዎችን በመሀል በመሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ:: **ድህረ ንባብ:-** ምንባቡን አንብበው የትወናው አካል እንዲሆኑ ማድረግ:: (ብዙ የተውኔት ጽሁፎች ያስፈልጋል) ተመሳሳይ የተውኔት ጽሁፎች እንዲያዘጋጁ ማድረግ :: ከጓደኞቻቸው ጋር የተውኔቱን ጽሁፍ እንዲተረጉሙ ማድረግ:: ከሌሎች ሰዎች ጋር ሀሳባቸውን ለመግለጽ ዘይቤያዊ አገላላጽ እንዲጠቀሙ ማድረግ:: የተለያዩ አያያገሮችን በጽሁፍ እንዲጠቀሙ ማድረግ ::	እንደሚጠቀሙ መጠየቅ